# የግብር ከፋይ ደረጃዎች

ግብር ከፋዮች፣ እንደሚከፍሉት ግብር መጠን በሦስት ደረጃዎች ይመደባሉ፡-

**1) ደረጃ “ሀ” ግብር ከፋይ**

የደረጃ "ሀ" ግብር ከፋይ የሚባሉት :- ድርጅቶች ወይም ጠቅላላ ዓመታዊ ገቢው ብር 1 ሚሊዮን (አንድ ሚሊዮን ብር) ወይም ከዚህ በላይ የሆነ ማንኛውም ሌላ ሰው ነው፡፡

**2) ደረጃ “ለ” ግብር ከፋይ**

የደረጃ "ለ" ግብር ከፋይ የሚባለው ድርጅትን ሳይጨምር ዓመታዊ ጠቅላላ ገቢው ከብር 1 ሚሊዮን (አንድ ሚሊዮን ብር) የሚያንስ ነገር ግን ከብር 500,000 (አምስት መቶ ሺ ብር) እና ከዚያ በላይ የሆነ፤

**3) ደረጃ “ሐ” ግብር ከፋይ**

ደረጃ "ሐ" ግብር ከፋይ የሚባለው ድርጅትን ሳይጨምር ዓመታዊ ጠቅላላ ገቢው ከብር 500,000 (አምስት መቶ ሺ ብር) የሚያንስ ሰው ነው፡፡

# መዝገብ አያያዝ

**የደረጃ “ሀ” ግብር ከፋዮች በፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ደረጃዎች መሠረት የተዘጋጁ የሂሳብ መዝገቦችን የመያዝ ግዴታ ያለባቸው ሲሆን፤ በተለይም የሚከተሉትን መዛግብት መያዝ አለባቸው፡-**

1) ቋሚ ሀብቶች የተገዙበትን ቀን፣ የተገዙበትን ዋጋ፣ ሀብቱን ለማሻሻል የወጣውን ወጪ እና የሀብቱን የወቅቱን የተጣራ የመዝገብ ዋጋ የሚያሳይ ሰነድን ጨምሮ የንግድ ሥራውን ሀብትና ዕዳ የሚያሳይ መዝገብ፤

2) ከግብር ከፋዩ ንግድ ሥራ ጋር በተያያዘ በየቀኑ የተገኘውን ማናቸውንም ገቢ እና ወጪ የሚያሳይ ሰነድ፤

3) ከንግድ ሥራው ጋር በተያያዘ የንግድ ዕቃዎችን ግዢና ሽያጭ እንዲሁም በግብር ከፋዩ የተሰጡ እና የተገኙ አገልግሎቶችን በተመለከተ የሚከተሉትን የሚያሳይ ሰነድ፤

ሀ) ለገበያ የዋሉትን ወይም የተቀበላቸውን የንግድ ዕቃዎች እና የተሰጠውን ወይም የተገኘውን አገልግሎት ዝርዝር፣

ለ) ከግብር ከፋዩ ላይ የንግድ ዕቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን የገዙ ወይም ለግብር ከፋዩ

ያቀረቡ ሰዎችን ስም እና የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር (እንደ ሁኔታው)፣

ሐ)የአቅራቢውን የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የያዙ አስቀድሞ ቁጥር የተሰጣቸው ደረሰኞችን፣

4) በግብር ዓመቱ መጨረሻ በግብር ከፋዩ እጅ የሚገኙ የንግድ ዕቃዎችን ዓይነት፣ መጠንና ዋጋ እና የዋጋ መገመቻ ዘዴን የሚያሳይ ሰነድ፤

5) የግብር ከፋዩን የግብር ኃላፊነት ለመወሰን የሚያስችል ሌላ ማንኛውምሰነድ።

**የደረጃ "ለ" ግብር ከፋዮች የሚከተሉትን ሰነዶች የመያዝ ግዴታ አለባቸው፡-**

1) የየቀኑን ገቢ እና ወጪ የሚያሳይ መዝገብ፤

2) ሁሉንም ግዥዎችና ሽያጮችን የሚያሳይ መዝገብ

3) የደመወዝንና የአበሎች መዝገብ፤

4) የግብር ከፋዩን የግብር ኃላፊነት ለመወሰን የሚያስችል ሌላ ማንኛውም አግባብነት ያለው ሰነድ፤

የደረጃ "ሐ" ግብር ከፋዮች ግብር የሚከፍሉት አማካይ የቀን ገቢያቸው ተገምቶ፣ የኢትዮጵያ ገቢዎች ባለስልጣን ባስቀመጠው ቀመር መሰረት ነው፡፡ከዚህ መደብ ሥር ያሉ ግብር ከፋዮችን የሒሳብ መዝገብ እንዲይዙ ማድረግ ለግብር ከፋዮቿም ሆነ መንግስት ግብርን ለመሠብሠብ የሚያደርገውን ወጪ በእጅጉ ያበዛዋል፡፡ ለዚህም ነው በቀን ገቢ ግምት ላይ የተመሠረተ ግብር እንዲከፍሉ የሚደረገው፡፡ ቢሆንም ግን ደረጃ "ሐ" ግብር ከፋዮች ጠቅላላ የሽያጭ ገቢያቸውን የሚያሳይ ወይም ሌላ አስፈላጊ መዝገብ ሊይዙ ይችላሉ።

**በተጨማሪ፣ ከቤት ኪራይ ገቢ የሚያገኙ የደረጃ "ሀ" ወይም "ለ" ግብር ከፋዮች የሚከተሉትን ሰነዶች የመያዝ ግዴታ አለባቸው፡-**

1) ከኪራይ የተቀበለውን ገቢ የሚያሳይ ሰነድ፤

2) ከቤቱ ጋር በተያያዘ ለመንግሥት ወይም ለከተማ አስተዳደር የተከፈሉትን ክፍያዎች የሚያሳይ ሰነድ፤

3) ከቤቱ ጋር ተያይዞ የሚወጣውን ማንኛውንም ወጪ የሚያሳይ ሰነድ፤

4) የሚከራየው ሕንፃ የተገኘበትን ቀን፣ ሕንፃው የተገኘበትን ዋጋ፣ ሕንፃውን ለማሻሻል የወጣውን ወጪ እና የህንፃውን የወቅቱን የተጣራ የመዝገብ ዋጋ የሚያሳይ ሰነድ፤

5) ቤቱን በሚመለከት የተደረገ ማንኛውንም የተከራይ አከራይ ስምምነት የሚያሳይ ሰነድ፤

Samuel Girma 0911190299